# ይመጣል ያልነው ቀን

ኋላ ቀርነቱን የጭቆናን ቀንበር ግፍና ሰቀቀን
አብዮት ቀስቅሰን ሥርዓት ለውጠን በትግላችን ፍቀን
ፍትህ ዕኩልነት . . . በረዥሙ አልመን ራኢይ ሰንቀን
በአብርሆት ተስፋ ዛሬን ልንኖረው ትናንትን ሸኝተን
ሆ ብለን ቼ ብለን ነጻነት ልናበስር ለህዝብ ቃል ገብተን
በዱር በከተማ ክቡር ህይዎት ሰጥተን ይመጣል ያልነው ቀን
ዛሬ መጣሁ ሲለን ነገ መጣሁ ሲለን ድል እየሰነቀ
ያለምነው ራኢይ የነገው ብሩህ ቀን ሄዶ ሄዶ አለቀ።

ይመጣል ያልነው ቀን ከሞት ተጎዳኝቶ
ህብስቱን ንጉሤን ጌትነትን ጠርቶ
ወንድማገኝንም ታዬ ቶላን በልቶ
ዛሬ ሲል ነገ ሲል ድል እየሰነቀ . . የኋላ የኋላ
ሄዶ ሄዶ አለቀ ጌዜ እየተሸኘ በሞት ሠረገላ።

ይመጣል ላልነው ቀን ብርቅየ ብርቅየው ስንት ወጣት ዕረግፎ
በህይዎት ለተረፍነው ፀፀቱን ቁጭቱን ንዴቱን አግዝፎ
በነበር ሲወሳ የክሩቤል ገድል የያ ትውልድ ህይዎት
ቆዝመን ስናየው ሆድ ሀዘን ይበላል ተስፋው ጥሎት ሲሞት።

የካቲት 2009

ለጓድ ክሩቤል መታሰቢያ
አብርሃም በየነ